# ስለ ቅዱሳት መጻሕፍትና
# ሳይንስ ስምምነት ።

ከዶክተር ኼሪ ሪመር
(D. D., Sc. D.)
ተደረሰ ።

ከጐበዜ ጣፌጠ
ወደ አማርኛ ተተረጎመ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በኻያ ዘጠኝኛው
ዓመተ መንግሥት ይህ መጽሐፍ ታተመ ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፱፻፵፫ ዓ· ም.

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

www.ethiopianorthodox.org

# መ ቅ ድ ም ።

የዚህ ስለ "ሳይንስና ቅዱሳት መጻሕፍት ስምምነት" ተብሎ የተዘጋጀው መጽ
ሐፍ ደራሲ ዶክተር ኼሪ ሪመር በመንፈሳዊና በዓለማዊ ትምህርት የሊቅነት ችሎ
ታው ተመስክሮ የተመረቀ ታላቅ ሊቅ ነው ።

የሚታየውንና የማይታየውንም ሁሉ በቃሉ ስለ ፈጠረው አምላክ ታላቅነትና
ሕያውነት ተመራምሮ ይህ በዘመን ብዛት የተጠራቀመው ዓለማዊ ጥበብና ቅዱ
ሳት መጻሕፍት በኅብረት ወይም ጐን ለጐን ሊኀዳኙ የሚችሉበትን መንገድና
ስምምነታቸውን በማይካድ ማስረጃ ገልጿል ። አስደናቂ የሆነው ዘመናዊው ጥበብም
ምን እንደሆነ አብራርቶ በመጽሐፉ አስረድቷል ።

ከዚህም የተነሣ ዘመናዊውን ጥበብና መጽሐፍ ቅዱስን በየፈርጃቸው ያስማ
ማው ሊቅነቱ በዘመናዊው ጥበብ እርምጃ ይዞታ በዚህ መጽሐፍ እንደ ተገለጠው ሁሉ
አንዳንድ በዓለማዊ ትምህርት ጠቢባን ነን የሚሉ ሰዎች ወይም የሳይንስ ሊቆች
ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማጣረስ ቢጥሩም ቅሉ ዘላለማዊውን የአምላክ ቃል ሊያ
ሻሽሉት ወይም ሊሽሩት አልቻሉም ፤ አይችሉምም ። ስለዚህ የቅዱሳት መጻሕፍ
ትን መሠረቶችና ታላቅነት በዘመናዊው ትምህርት መራቀቅ ማለት የሰው ሥራ
ውጤት (ሳይንስ) እንደማያነቃንቀው የታመነ ነገር ለመሆኑ ይህ መጽሐፍ አብራ
ርቶ በማስረዳት ፤ ሳይንስ ነክነት ባላቸው ጉዳዮች መነሻነት በደራሲው ላይ የቀረቡትን
ክርክሮች ሁሉ እንዳቀራረባቸው ተገቢውን መልስ በመስጠት ያስረዳል ።

ልዑል እግዚአብሔር በራሱ ሥልጣንና ፈቃድ የፈጠራቸው በግዘፍ የሚታ
ዩትና ከረቂቅነታቸው የተነሣ ለዓይን የማይታዩት ኢምንቶችም ሁሉ በትምህርት
ብዛትና በዕውቀት መስፋፋት ምክንያት ተገጣጥመው ዛሬ ሰውን የሚያገለግሉት
የትምህርት ሥራ ውጤቶች ሁሉ ከፈጣሪያቸው ጋር ስምም ስለ መሆናቸው ቅዱ
ሳት መጻሕፍት ያረጋግጣሉ ። እጅግ በጣም በመራቀቅ የመረመሩት አንዳንድ ሊቆ
ችም ስለ ታላቅነቱ ሲያስቡ የእነሱ ችሎታ በሐይቅ ዳር እንደሚንቦጫረቁ ሕፃናት
ለመሆናቸው ራሳቸውን ይቆጥራሉ፤አሁን ስለምንገኝበት ዘመንም አስቀድሞ በመንፈስ
ቅዱስ ትንቢት ተነግሮ እናገኛለን ። ትንቢቱም "አንተ ግን ዳንኤል ሆይ ፤ ነገሩን
ዝጋ መጽሐፉንም አትም እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ብዙዎች ይመረምራሉ ዕው
ቀትም ይበዛል" ይላል ። ዳንኤል ፲፪ ፡ ፬ ።

ይህ ትንቢት ከተተነበየ አንሥቶ እስከ አለንበት ኻያኛው መቶ ክፍል ዘመን
ድረስ ቢቆጠር ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ያህል ነው ። በ፲፱ኛኛውና
በኻያኛው መቶ ክፍለ ዘመናትም ታላላቅና አስገራሚ የሆኑ ጥበቦች በትምህርትና
በመመራመር ብዛት ለሰው ልጆች ተገልጠዋል ።

የሰው ልጆች አእምሮም አስቀድሞ እንደ ተተነበየው ሁሉ በዘመን ብዛት ጠልቆ
መመራመርን ስላበዛና የተፈጠሩትንም ነገሮችና ኢምንቶች በትምህርት ውጤት መሠ

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ በመሠረታዊ ቁም ነገር ሁሉ የብሉይ ኪዳን ሕገ ልቡና ግጻጅ የአዲስ ኪዳን ሕገ ልቡና ግጻጅ ሆኖ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተብራርቶ እናገኘዋለን ። ጌታችን ሥጋን ለብሶ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ በራሱ መሥዋዕትነት ከተሻሩት ነገሮች በቀር ሌላ የተሻረ ቁም ነገር ወይም ሕገ ልቡና አይገኝም ።

(የሐዋርያው የጳውሎስ ወደ ዕብራውያን የተጻፈው መልእክት ስለ ብሉይና አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ኅብረት በጉልህ ያስረዳናልና እንብቡት ።)

«የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን ። አሜን» ፪ኛ ፡ ቆሮ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

ጉበዜ ጣፈጠ ።

---

## መ ግ ቢ ያ ።

ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኝነትና ትክክለኝነት የክርስቲያንን ሃይማኖት ለማጣረስ ስለሚቀርቡት ነቀፌታዎች አብራርቶ ለማስረዳት በመቶና በሺህ የሚቆጠሩ አድማጮች በተገኙባቸው አደባባዮች በንግግር መልክ በዚህ መጽሐፍ የሚገኙት አርእስተ ቁም ነገሮች ንግግር ተደርጐባቸዋል ።

ከእንዚሁ አርእስተ ቁም ነገሮች ጥቂቶቹም በብትን ጽሑፍ መልክ ተራብተው በብዙ መቶና ሺህ ቅጆች ታድለዋል ።

ደራሲውም እነዚህን ብትን የሆኑ ጽሑፎች እንደገና መርምሮ ካስተካከለ በኋላ በመጽሐፍ ቅርጽ ተጠርዞ እንዲታተም የአደረገንበት ምክንያት እንደዚህ ያሉት ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት እውነተኝነትና ትክክለኝነት የሚያረጋግጡ መጻሕፍት በየቤተ መጻሕፍቱና በየትምህርት ቤቶች ሁሉ እንደ ልብ እንዲገኙ በማሰብ ነው ።

ይህ ያሁኑ መጽሐፍ በቅደም ተከተል ለወደፊት ከሚታተሙት ስድስት መጻሕፍት መጀመሪያው ነው ። እነዚህ መጻሕፍትም ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት በሳይንስ ይዞታ በኩል የሚቀርቡትን ነቀፌታዎች ከንቱነትና ክርስቲያኖች በቅዱሳት መጻሕፍት ያሉአቸውን ግልጥ የሆኑ ማረጋገጫዎች አብራርተው የሚያስረዱ ሲሆኑ መጻሕፍቱም ለዮሐንስ ሎሬንስ ፍሮስት መታሰቢያ የሚበረከቱ ናቸው ።

ይህ ጐልማሳም በልዩ ልዩ አደባባዮች አንድ ክርስቲያናዊ ተማሪን የሚጋጠሙት ፈተናዎች ሁሉ ደርሰውበት በክርስቲያናዊ የመንፈስ ብርታት በማያወላውል ሁኔታ ድል የነሣ ወጣት ነበር ። በስታፎርድ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ገበታ ላይ ሳለ ትምህርቱን በማከናወን ተመርቆ መክሊቱን ከሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት በሞት እንቅልፍ ተጠርቶ ከክርስቶስ ጋር ይኖር ዘንድ አርፎአል ።

ወላጆቹም ስለ እሱ ክርስቲያናዊ ኑሮ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ እንደዚህ ያለው መታሰቢያ እንዲቆምለት ፈቀዱ ። ይህን የሚያደርጉትም ለልጃቸው መታሰቢያነት ብቻ ሳይሆን የእሱ ክርስቲያናዊ ዝንባሌ በሺህ በሚቆጠሩ ሌሎች ሕይወቶችም ደግሞ እንዲታዩ በመናፈቅ ነው ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጻፉት ቃላትም ደራሲው በቅርብ ያውቀው ስለነበረ ክርስቲያናዊ ሕይወት የደስታን መግለጫ ያህል ሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተገለጠው ሁሉ በእግዚአብሔር ጸጋ መለወጥ ስለሚችሉት ሕይወቶች ጭምር እንጂ ለእሱ ብቻ የሚበረከቱ አይደለም ።

ኬሬ ረመር ።

www.ethiopianorthodox.org

የተጻፉትን ቃሎች በሰው ሠራሽ መሣሪያዎች አማካይነት ፤ የመሣሪያዎቹን ቁልፎች በጣት ተጭኖ ባንድ ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ለየቀበሌዎችና ክፍለ ሀገሮች ሁሉ፤ ፩ የሚጻፍ ደብዳቤ ከመድረቁ በፊት ለመበተን መቻል ፤ ይህ የሰብአዊ ፍጡር ሥልጣኔ የቱን ያህል እንደ ተራመደ ለመረዳት አያዳግትም ፤ አይከድምም ።

ኢዮብ በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች "እናንተ ከጥበባችሁ ጋር የምትጠፉት ሰዎች ናችሁ" ብሎ የተናገረው አስቀድሞ ስለ ተረዳው ነው ። ኢዮብም እስከዚህ ትውልድ ዘመን ድረስ በሕይወተ ሥጋ ተገኝቶ ዛሬ ይኸኑ ቢናገር ኖሮ ፥ ይህ እኛ የደረስንበት ሥልጣኔ እሱ እንዳለው መሆኑን በመረዳት በእርግጥ ቃሉን እንቀበለው ነበር ። ይህ ሁሉ ከተባለና ከተፈጸመም በኋላ በሕሊናችን ውስጥ አንድ አስታዋሽ ነገር ይደቀንብንና ጥንታውያን ነገሮች ሁሉ ብልሹ ኪነ ጥበባት ናቸው ማለትም ይቀል ይሆናል ።

ስለ ሰዎች መሐንዲሳዊ ብልሃትና ጥበብ ሲነገርም ፤ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ጥንታውያን ሥራዎችን በማሰላሰልም ደግሞ ክርናክንና ሮም ላይ የነበረውን ታላቅ የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ የዘመኑን ኀብኚዎች ናፍቆት በአድናቆት መማረክ የሚችሉትን ፍራሾች መንብኘት ይበቃል ።

ስለ ጥርብ ደንጊያ ፍጽምና ሲነገርም ፤ ፊዲያስ የተባለውን ሰው ስም በአድናቆት ያወሳሉ ። በሰዓሊነት ረገድም ድምጾች ሁሉ ጥንታውያን ሰዓሊዎችን በአክብሮት ስለሚያወሱ ፤ በንዳንድ ነገሮች ረገድ ደግሞ ሥልጣኔአችን ወደ ኋላ የተመለሰ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ሰውም ፤ በጥንታዊ ምሥጢራዊ ነገር ፊት ራሱን በትሕትና ደፍቶ መቆም የሚገባው በጥንታውያን ጥበበ ቃላት ፊት ነው ።

በግምት ከሁለት ሽህ ዓመታት በፊት ከቅዱሳት መጻሕፍት የመጨረሻው ጸሐፊ ብርዕ አርፎአል ። በእነዚህ ረዥም ተከታታይ በሆኑ ዓመታት ጊዜያትም ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዲት ቃል ስንኳ ተጨምራ አትገኝም ። ዳሩ ግን እጅግ በጣም ብልሆችና ጠቢባን ሰዎችም ሳይቀሩ ወደዚሁ ወደ ታላቁ ጥንታዊ መጽሐፍ የጥበበ ቃላትን ምሥጢሮች ለማግኘት ሲሉ ፊታቸውን ይመልሳሉ ።

በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ከሠፈሩባቸው ታላላቅ አስገራሚ ነገሮችም ፤ አንዱ ዛሬ በሳይንስ የሥልጣኔ እርምጃ የወጡትን ነገሮች ፤ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች አስቀድመው ትንቢት መናገር መቻላቸው ነው ።

አንድ ልበ ቅን የሆነ ተመራማሪም ስለ ሳይንስና ቅዱሳት መጻሕፍት ስምምነት መርምሮ ለመረዳት ቢፈቅድ ፤ እነዚህ መሠረታውያን ቁም ነገሮች ችላ ሊባሉ አይገባም ። አሁን በመራቀቅ እያደገ የሚሄደው ጥበባችን ከመጠራቀሙ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ የተጻፈ በመሆኑ የፍጡር ጥበብ ይህን መጽሐፍ ከሚያድገው ጥበብ ጋር ስምም ይሆን ዘንድ ጠብቆታል ማለትም በፍ



ጹም የማይታሰብ ነገር ነው ። ስለዚህ በዘመናችን በሳይንስ ምርመራ ረገድ በመመርመሪያ ክፍል ውስጥ ፤ አንዳንድ አስደናቂ አዳዲስ ነገሮችን መፈልሰፍና ማብራራት ስንችልና ጥንታውያን ጸሐፊዎችም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለ ጥበቡ ጉዳይ አስቀድመው ጽፈውት ሲገኝ ፤ ራሳችንን በአስቸጋሪና ግራ አግቢ በሆኑ ቀንዶች መኻል እንገኛለን ።

እንግዲህ ጥንታውያን ሰዎች ዛሬ እኛ የጨበጥነውን ሳይንሳዊ ዕውቀት ጨብጠው ነበር እንበል ? ። ይህ ጥበብ ነበራቸው ብለን መናገር አንችልም ። ከሁሉ አስቀድሞ የኛ የዕውቀት ጥበብ አካል ፤ ዛሬ ጐልቶ የሚታየው በዘመናት ብናት ጥቂት በጥቂት ሲል በታላቅ ተጋድሎ ጥናትና ምርመራ የተጠራቀመ መሆኑ ሲታወቅ ፤ በእነዚህ ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት በተመዘገቡባቸው ጨለማ ዘመናት ከነበረው ድንግዝግዝ የሆነ ዓላማዊ ዕውቀት በጣም የሚበልጥ ነው ።

ያለምንም መጠራጠርም የዛሬው ከፍ ያለው የሞላ ጐደል እውቀታችን አቋም በታላቅ ምርመራ የተገኘ የቅርብ ዓመታት ቅርስ ነው ።

ይህ ሁሉም እውነተኝነቱ በተጨበጠ መረጃ ሊገለጽና ሊታይ የቻለው ደጋግሞ በመመርመርና በማጣራት መሆኑ የሚካድ አይደለም ። አየርስ የተባለው ሊቅ እንዳስረዳው ሁሉ የዘመኑ ጥበብ እንዲህ መስፋፋት የቻለው የመኪና ብልሃት በመፈልሰፉ ምክንያት ነው አለ ። አየርም እንዲህ ማለቱ ብልሃቱን ብቻ ለመግለጽ ሳይሆን የዘመኑ ምርመራና ጥናት ሁሉ ተፈላጊውን መሣሪያ አገጣጥሞ በመገልገል መሆኑን ጭምር ማስረዳቱ ነው ።

ስለ ነፍሳት ሁኔታ በሚያጠናው ጥበብ (ባዮሎጂ) ረገድ የተደረገው ታላቁ እርምጃ ምንድን ነው ? ለዚህም ጥያቄ መልሱ በደም ሥሮች ስለ ደም ተግባር ጉዳይ ማወቂያ የወጣው ጐልጅ የተባለው መሣሪያ በመገጣጠሙ ነው ትሉ ይሆናል ። እንግዲህ መልሳችሁ ይህ ከሆነም ተሳስታችኋል ማለት ነው ፤ በነፍሳት ምርመራ ረገድም ጐልጅ የተባለውን መሣሪያ ለሰብአዊ ዓይን አጉልቶ የሚያሣየው መነጽር በመፈልሰፉ ነው ።

እንደዚህ ያለውን መሣሪያ በእጃችን ስንጨብጥ ፤ በመሣሪያው አማካይነት ሊታዩ የሚገቡትን ነገሮች በትክክል ማየት እንችላለን ። በኪነ ጥበብ (ፊዚክስ) ረገድም ደግሞ የተደረገው ታላቁ እርምጃችን አቶም እንዲለይ መደረጉ ብቻ ሳይሆን ለምርመራው ይረዳ ዘንድ ለመለየት ወይም ለመክፈል ከፍተኛ ኤክስሬይና አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር መፈልሰፉ ጭምር ሆኖ ፤ አቶምም በሰው አእምሮ ሊመጠን በመቻሉ ነው ፤ ሰዎችም አርቆና አጉልቶ የሚያሣይ መነጽር (ቴሌስኮፕ) ሲኖራቸው የፀሐይ ከነሠራዊቷ ሁናቴ በሕሊናቸው ይቀረጻል ፤ አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር እስከ ተፈለሰፈበት ዘመን ድረስም ፤ ስለ ረቂቃን ትላ ትሎችና ተውሳኮች ሁናቴ ማጥናትና ስለመኖራቸውም ሰዎች ማወቅ አይችሉም ነበር ። የዘመኑ ሥልጣኔአችንም በተፈላጊዎቹ መሣሪያዎች መገጣጠም የተማመነ በመሆኑ በጥንታው

www.ethiopianorthodox.org

ከብዙ ሰዎች መኻል ግን በመቶ አሥሩ ስንኳ አንብበውት አይገኝም ። ይህ መጽሐፍም ከሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ይልቅ ፤ ይበልጥ የውይይት መለዋወጥ ተደርጎበታል ።

ከክርስቲያን ወገኖችም ክርክሩ ስለምን እንደሆነ ጠንቅቆ ለመገንዘብ ያህል በጽሞና አንብበው ከመቶ አሥሩ ስንኳ ጊዜአቸውን አላሳለፉበትም ፡ ዘመናውያን ነቃፊዎችም ሳይቀሩ ከዚሁ መጽሐፍ ሁለቱ ጥቅሶች ቢገደፉ ይቀበሉታል ። «እነዚህ ሁለት ቍጥሮች ባይመዘገቡበትና ባይበላሽ ኖሮ መጽሐፉ ታሪካዊ ቅርስ ይሆን ነበር» ፤ ሲሉም ይሰማል ።

እነዚህ አከራካሪ ጥቅሶችም በእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ምዕራፍ መጨረሻ ቍጥርና ሁለተኛው ምዕራፍ መጨረሻው ቍጥር ናቸው ።

(በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሁለተኛው ምዕራፍ መጀመሪያውና መጨረሻው ቍጥሮች ናቸው) ። ሕዝበ ነነዌ ከፍ ያለ አመፅ ስላደረጉ የአምላክ ቁጣ በሕዝበ ነነዌ ላይ መንደዱን መጽሐፈ ዮናስ መጀመሪያው ምዕራፍ ይተርካል ።

አምላክም ለቁጣ የዘገየ መሐሪ አምላክ በመሆኑ ዮናስ ወደ ሕዝበ ነነዌ ሄዶ ስለ ኃጢአታቸው እንዲያስጠነቅቃቸው አምላካዊ መልእክት ደርሶት ነበር ። ንስሐ ካልገቡ በቀር ከተማዋም ከነነዋሪዎቿ ጭምር አብራ የምትጠፋ ለመሆንዋ መልእክቱን ሊያደርስ ነበር ። ዮናስ ግን ወደ ነነዌ በመሄድ ፈንታ በተላላፊ መርከብ ተሳፍሮ ወደ ተርሴስ ጉዘውን በቀጠለ ጊዜ ከነነዌ አቅጣጫ ተቃራኒ ነበር ። ነገር ግን እግዚአብሔር ካዘዘው ተግባር ለማምለጥ በመሸቱ ኃይለኛ ነፋስ ተነሥቶ መርከቢቱንና ሌሎች ተሳፋሪዎችንም አስጨነቀ ። ተሣፋሪዎችም ይህ መዓት የደረሰባቸው በዮናስ ምክንያት መሆኑን ስለ ተረዱ በፈቃዱ ከመርከቡ አውጥተው ወደ ባሕር ጣሉት ። እንዲህም ያደረጉበት ዋናው ምክንያት ራሳቸውን ለማዳን ነበር ። የታሪኩ ማጠቃለያና አከራካሪም «እግዚአብሔር ዮናስን ይውጥ ዘንድ ታላቅ ዓሣ አሰናዳ ። ዮናስም በዓሣው ሆድ ሦስት ቀንና ሌሊት ተቀመጠ» ፤ ወደሚለው መግለጫ ያደርሰናል ። ሁለተኛው የሚያከራክረው ጥቅስም ፤ በሁለተኛው ቍጥር ላይ «ዮናስም ከዓሣው ሆድ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ወደ አምላኩ ጸለየ» የሚለው ነው ። ማንም አስተዋይና ብልህ የሆነ ሰው በዚህ መግለጫ ምንም ስሕተት ማግኘት አይችልም ። እዚህ ላይ ያለው አስገራሚው ነገር ግን ይህ ሐሳበ ግትር የሆነው ነቢይ ወደ አምላኩ ጸሎት ከማድረግ ሦስት ቀኖች ያህል ዝም ማለቱ ነው። ከመኻላችን አንዳችን በእንደዚያ ያለ ዓሣ ብንዋጥ ኖሮ ከሦስት ደቂቃዎች በፊት ጸልየን አምላክም ጸሎታችንን በሰማ ነበር ። ተዋጨም ወደ ነነዌ እሔዳለሁና ከዚህ አውጣኝ ብሎ ይወተውት ነበር ። ሐሳበ ግትር ነቃፊው ዮናስ በዓሣው ከርሥ ሳለ ስለ መጸለዩ ምንም ጥያቄ አያቀርብም ። በዮናስ በኩል ግን ማንም ቢሆን ወደ አምላክ መጸለይ ይገባው ነበር ።

ከዚሁ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ቍጥሮች የዮናስን ጸሎት የሚመለከቱ ሲሆኑ አሥረኛውና የመጨረሻው ቍጥር ግን ክርክር የሚነሳባቸው ናቸው ። ይህ መግለጫም ከዚህ በሚቀጥሉት ቃላት ተገልጿል ።



"እግዚአብሔርም ዓሣውን አዘዘው እርሱም ዮናስን ወደ ደረቅ አውጥቶ ተፋው» ይላል ። በዚህ ጥቅስ ላይ ምንም ዓይነት ትችት ለማድረግ ሳንሞክር በደንብ ታርሞ ከተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል ትርጕሙን ጠቅሰናል ። ይህ ጥቅስም በብዙ ሰዎች ዘንድ በጣሙን የታወቀ ነው ።

ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮም መናፈቅ የሚሳልቅበት ጥቅስ ይኸው ነው ። ይህም መናፍቅነት ሊያስተባብለው ያልቻለ እውነተኛ የሆነ ታሪክ መሆኑን ደግመን እናስረዳለን ።

የነቢዩ ዮናስ ጠባይ በጣም አስገራሚ ነው ። የከፍተኞች ትምህርት ቤቶች ነቀፌታዎችም፤ አምላክ ከሰው ጋር ያለውን አግባብነት በመካድ ብቻ የዓሣውን ታሪክ ይቀበሉት ዘንድ አይፈቅዱም ። ስለ ተአምሩ መግለጫ የሆኑትን ሁለቱን ጥቅሶች ብንደመስሳቸው መጽሐፉ ለእነሱ ስሜት የሚገባ ነው ብለው ይቀበሉታል ። ዳሩ ግን በየዘመነ ትውልዱ ሁሉ የሚወጣውን ልዩ ልዩ ሐሳብና ፍላጎት ለማጥገብና ለየዘመነ ትውልዱ ሐሳብ ተስማሚ ይሆን ዘንድ ሲጀመር ጀምሮ የተመዘገበውን የአምላክ ቃል ለመለወጥ ጠቃሚና ተፈላጊ አይሆንም ። አምላክ እንደ ጻፈው አድርገን ይህን መጽሐፍ እንቀበለው ዘንድ አስፈላጊነቱ ግልጥ ነው ። የእኛም ዕውቀት ከእራሱ ራዕይ ጋር ስምም መሆን ይገባዋል ።

ለላቀው ለመንፈስ ቅዱስ ጥበብ በትሕትና ለመንበርከክ ፈቃደኛ ባለመሆን ዮናስ ለመኖሩም ታሪኩን በፍጹም ይክዳሉ።ሄራኩለስ በግሪኮች አፈ ታሪክ እንዳለ ሁሉ ፤ «የዮናስ ታሪክም አይሁድ በምድኟ ዳር ወጋቸው ፤ ያወጉት የነበረ ያንድ ጀግና ልብ ወለድ ታሪክ ነው እንጂ እንደዚህ ያለ ዮናስ ከቶ አልነበረም» ብለዋል ።

የሆነ ሆኖ የዚሁ ተቃራኒ እርግጠኛ የሆነ ነገር ነው ። ናፖሊዎን በናባርትና ዳግማዊ ራምሴስ እንዳላቸው ታሪክ ሁሉ ፤ ዮናስም ደግሞ እንደዚሁ ታሪካዊ ሰው ነው ። የእነሱ እውነተኛ ታሪክም በተጣራና ሊታመንበት በሚቻል መጽሐፍ ውስጥ ይገኝ ይሆናል ።

በአምላክ መንፈስ መሪነት ዕብራውያን ነቢያት መዝግበውት ለእኛ ከደረሰው ዜና ነገሥታት መጻሕፍት የሚበልጥ ስለማንኛውም ሕዝብ ተጣርቶ የተጻፈ መጽሐፍ አይገኝም ። በዘመናችንም ምድርን ቆፍሮ ታሪካዊ ቅርስን የሚያበረክተው ጥበብ (አርኪዮሎጂ) ምንም እንኳ ሌላ ነገር ማድረግ ባይችልም ቅሉ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትክክለኝነት ማጽደቅና ማሳመን ችሎአል ።

በመጽሐፈ ነገሥት ካልእ በ፲፬ኛው ምዕራፍ ውስጥ የዮናስ ታሪካዊ ሰው መሆኑን የሚገልጽ ጉዳይ ተመልክቷል ። ይህም ዮናስ ሥረ ወጥ ታሪክ ያለው ነቢይ መሆኑን ይገልጽልናል ። በዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት አንቀጽም የዮናስ አባት በስሙ ይወሳል ፤ ሐረገ ትውልዱም ተነግሮአል ፤ ይኖርበት የነበረው ሥፍራም ተወስቷል ። ዮናስ በሕይወተ ሥጋ በነበረበት ዘመን ይገዛ ስለ ነበረው ንጉሥ ስምም እንማራለን ። በዚሁ ንጉሥ ዘመነ መንግሥትም ዮናስ ከተናገራቸው ትንቢቶች

www.ethiopianorthodox.org

ሮች ሁሉ መፍጠር የቻለው አምላክ ነው» ። ስለዚህ ሙሴ ከቅዱሳት መጻሕፍት በመጀመሪያው መጽሐፍ በገለጸው ጽሑፍ ውስጥ አንድ ልዩ የሆነ ነገድን የሚመለከት ጥላ ከቶ አይገኝበትም ። ይህ ሁሉን ፈጣሪ የሆነው አምላክም ርኅሩኅና ደግ አምላክ መሆኑን እናገኛለን ። በመጀመሪያዎቹ ጽሑፎችም ከፈጠራቸው ፍጥረታት ጋር በኤድን ገነት ውስጥ ሲመላለስና ሲነጋገር እናገኘዋለን ። እንደዚህ ያለው ፍጥረቱን አፍቃሪ አምላክም በዚያን ጊዜ ከፍጥረታቱ ጋር የነበረው ግንኙነት በመቸም ጊዜ ታይቶ አይታወቅም ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ስንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ „ስትጸልዩም አባታችን ሆይ ፤ ብላችሁ ጸልዩ„ ፡ አለበት ጊዜ ድረስም በቅዱስ መንፈሱ ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርግ ነበር ።

መድኃኒታችንም እግዚአብሔር አባት መሆን የሚችለው ለሚወዱትና ለሚያገለግሉት መሆኑን በጥንቃቄ አስረድቷል ። ለእግዚአብሔር መልእክት ጠላቶች ለነበሩትም ኢየሱስ «እናንተ የአባታችሁ ልጆች ናችሁ ፤ ያባታችሁንም ሥራ ታደርጋላችሁ› አላቸው ።

ስለዚህ የከፍተኛ ነቃፊ ወገኖች ሐሳቦች ሁሉ ምንም መሠረት የላቸውም ማለት ነው ። መሠረተ መነሻቸውም ሐሰት ነው «እግዚአብሔር የአንድ ነገድ አምላክ በመሆኑ ብቻ ተከታዮቹ ሐሳቡን አስፋፉለት ወይም ደግሞ እግዚአብሔር የሞላው ዓለም አባት ነው የሚሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም› ሲሉ የሚከራከሩበት ረድፍ ዋጋ ቢስ ሆኖ ይገኛል ።

ተቃራኒ ትምህርት ቤቶችም ከሚያቀርቡአቸው ክርክሮች ፤ አንዱ ኃይለኛው ክርክር ስለ ዮናስ ጠባይ ነው ። ‹እግዚአብሔር ለአንድ ለተለየ አገልግሎት በጠራው ጊዜ ከአምላክ ጥሪ ኰብልሎ ወደ ተርሴስ አመራ› ይላል ። እዚህም ላይ ብርቱው ተከራካሪ የሚለው «ዮናስ ፤ የእግዚአብሔር ሥልጣን በፓለስቲን ብቻ የተወሰነ መሆኑን ያምን ስለነበረ ፤ ስለዚህ ከፓለስቲን ክልል ከወጣ በኋላ የእግዚአብሔር ኃይል ሊደርስበት ስለማይችል ኰበለለ» ይላል ።

ስለ ዮናስ እምነት ጉዳይ ስንመረምር ግን ይህ ከዚህ በላይ የተሰነዘረው መንቀፊያ ሐሳብ ከእውነት የራቀ ሆኖ ይገኛል ።

ዮናስ በአምላክ ላይ ስለ ነበረው እምነት የማያምን ፤ መናፍቅና ከሐዲ ወይም ኃይለኛ ነቃፊም በዚህ በተማታ እስትያየቱ ምንም ድጋፍ ማግኘት አይችልም ። ምክንያቱም ዮናስ ዓለምን በሞላ በሚገዛውና ሁሉን ቻይ በሆነ አምላኩ ያምን ስለ ነበረ ነው ። ስለዚህ የዚህን የታወቀ መጽሐፍ መጀመሪያውን ምዕራፍ ጠንቅቃችሁ ብታነቡት አውሎ ነፋስ በኃይል ሲነፍስ ሳለና ተሳፋሪዎቹም ተጨንቀው በነበረበት ጊዜ ዮናስ በሰላምና በፀጥታ እመርከቢቱ ላይ ተኝቶ ነበር ። የመርከቢቱ አለቃም ከእንቅልፉ ቀስቅሶ «ማነህ»? ብሎ በጠየቀው ጊዜ ዮናስ የሰጠው መልስ ልባዊ እምነቱን በትክክል ይገልጻል ። እንደገናም አስገራሚ ቃላቱን ልብ አድርጓቸው ። ‹እኔ ዕብራዊ ነኝ አላቸው ፤ ባሕሩንና ደረቁን የፈጠረውን እግዚአብሔርን የሰማይን አምላክ አመልካለሁ» ፤ ብሎ ገለጠላቸው ። ዮናስ ፩-፱ ።



ይህ ጥቅስስ የሚያስረዳው የዮናስ ልባዊ እምነቱ ማረጋገጫ ፤ እግዚአብሔር የአንድ ነገድ አምላክ መሆኑን ብቻ ነው? ወይስ ደግሞ እግዚአብሔር የፓለስቲን ክፍለ ሀገር አምላክ ለመሆኑ ብቻ ነው? ። ይህ አንድ ማረጋገጫ ነው ። ዮናስ ፈጣሪ በሞላ ዓለም ላይ ገዥ መሆኑን ተገንዝቡአል ። እሱ ወደ ማይደርስበት አገር ኰብልሎ ለማምለጥ አለመቻሉንም ያረጋግጣል ።

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ „እግዚአብሔር የማይደርስበት ቦታ ከሌለ እንግዲያውስ ዮናስ ስለምን ወደ ተርሴስ ለመኰብለል ታገለ? ከነነዌ ወደ ሌላ አቅጣጫ በምትሄደው መርከብስ ስለምን ተሳፈረ„ ? የሚል ነው ።

ዮናስም እንደ ሌሎቹ እሥራኤላውያን ነቢያት ሁሉ በሀገር ፍቅር የተነደፈ ነቢይ መሆኑን እናስታውስ ። -እሱም ወገኖቹንና ሕዝቡን በጣም ይወዳቸው ነበር ። በዚያን ዘመንም ሕዝበ ነነዌ የእሥራኤል ጠላት ነበር ። ከእግዚአብሔርም ነነዌን ከነሕዝብዋ ንስሐ ካልገባች በቀር በፍጹም አጠፋታለሁ የሚል አምላካዊ ቃል ወደ ዮናስ በደረሰ ጊዜ «ይህ ሀሳብ ይስማማኛል ፤ እግዚአብሔርም ሕዝበ ነነዌን ከምድር ገጽ ቢያጠፋ ለእሥራኤል እንደ ታላቅ ድል ይቈጠራል ፤ ስለዚህ እኔም የተቻለውን ያህል ከምድረ ነነዌ ልራቅ» ብሎ ይሆናል ።

በሌላም አነጋገር ደግሞ ዮናስ እንደ ዘመናዊው ማንኛውም ሥጋ ለባሲ ስለ ነበረ ስለ ወገኑ ከፍ ማለት ሰብአዊ ፍላጎትና ስሜት አድሮበት ይሆናል ። እንደ ዚህ ያለው ስለ ሀገር ፍቅርና የወገን ጥቅም ማሰብም አብሮ የሚወለድ ትዝታ ነው ፤ በጣም በሠለጠኑት በአሜሪካ ክርስቲያን ሕዝቦች ላይ ፤ አሜሪካ በኻያኛ መቶ ክፍለ ዘመን ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በገባች ጊዜ ተገልጡአል ። በዓለም ሕዝቦች ዘንድ የወንድማማችነት መንፈስ እንዲጎለምስ የሚያስቡትና የሚወያዩት ክርስቲያኖችም ሳይቀሩ ፤ ጀርመኖችን መርገምና ንጉሡን (ካይዘርን) መወንጀልና ማሳጣት ጀመሩ ። ምክንያቱም የዚሁ የአሜሪካ ሕዝብ ጠላቶች በመሆናቸው ነው ። በእንደ ዚህ ያለ አጋጣሚ ጉዳይ ዘመናዊ የሆነ ሰው እንደሚሰማውና እንደሚያደርገውም ሁሉ ዮናስ እንደዚሁ ተሰምቶት አደረገ ማለት ይቻላል ።

እንደዚህ ያለው በዮናስ የደረሰበት ጥልቅ ስሜትም እሱን ወደ ዋጠው ዓሣ ታሪክ ያደርሰናል ። አምላክም ፤ ነቢዩ ዮናስ ካመፀበት ጊዜ ጀምሮ ንስሐ እገባበት ጊዜ ድረስ ይከተለው ነበር ። ከሁሉ አስቀድሞም ዮናስን በአውሎ ነፋስ ተከተለው ፤ ምክንያቱም አውሎ ነፋስ የተነሣው በእሱ ምክንያት መሆኑን ስለ መሰከረ ነው ። ስለዚህ ዮናስ በአውሎ ነፋሱ መነሣት ምክንያት አልተጨነቀም ነበር ፤ በሰጠውም መልስ የአምላክን ጠባቂነት አምኑአል ። በመርከቢቱ አለቃ አማካይነትም የአምላኩ ጥሪ ደርሶት ይከተለውም ነበር ። ከዚህም ሌላ ደግሞ ሰዎቹ ዕጣዎችን በጣሉ ጊዜ ዕጣው በዮናስ ላይ መውደቁ አምላክ እንደተከተለው ያስረዳል ። ዮናስን ከመርከቢቱ አውጥተው በጣሉት ጊዜ ከሰው አቅም በላይ የሆነ ነገር ጣልቃ መግባቱን የሚያስረዳው በታሪኩ ዮናስን እንዲያስተናግድ ከአምላክ ዘንድ አንድ ታላቅ ዓሣ ስለ መዘጋጀቱ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ፣ ይህ ወደ ዓሣው ታሪክ ያደርሰናል ። እያንዳንዱ ሰውም በግል አስተያየቱ የራሱን ፣ የሕሊና ዳኝነትና አስፈላጊውን ምርምር እንደሚያደርግ እንመኛለን ። የዮናስ ታሪክ ትክክለኛና እውነተኛ መሆኑን ተረድተን ለማስረዳት ስንጣጣርም ስለ ዮናስ ታሪክ የሚገባ ምርምር አላደረጋችሁም በመባል ክርክርና ነቀፌታ ይነሣብን ይሆናል ። እንዲህም የሚል ክርክር ቢነሣብን ፣ መልሳችን አስቀድመን የአምላካችንና የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምስክርነት በማንበባችንና የእሱንም ቃል ያለ ማመንታት ስለምንቀበለውና የሚናገረውንም ቃል ስለምናምን በት ነው ብለን እንመልሳለን ። ከኢየሱስ ምስክርነትም ሌላ የዮናስ ታሪክ እውነተኛ የሆነ ታሪክ ስለመሆኑ እናምናለን ፣ ምክንያቱም መናፍቃንና ከሀዲዎች ሐሳባቸውን በማማታት ስለ ሚክዱት ነው ። በእንደዚህ ያሉት ሰዎች ላይ የአእምሮ መናወጥ እንደደረሰባቸው እንረዳለንና የሚንቁትን ወይም ችላ የሚሉትን እንቀበለዋለን ። በዚህ ጥበባት ሁሉ ተራቅቀው በሚጠኑበት ዘመንም የክህደትና የመናፍቅነት ጠባይ ያላቸው ሰዎች በክህደት መንገድ በግል አስተያየታቸው ሕሊናዊ ምርመራ ለማድረግ አለመፍቀዳቸውንም ተረድተናል ። አንድ ከሃዲም አእምሮውን ሸፍኖ ስለ አንድ ቁም ነገር ለመመራመርም ሆነ ለማጥናት ሲጀምር የጥረቱ ውጤት የተዘበራረቀና የተማታ ይሆንበታል ፣ መናፍቅም እንደዚሁ ነው ።

የሆነ ሆኖ በዮናስ ላይ ስለ ደረሰው አስገራሚ ታሪክ ከአምላክ ሥልጣን በቀር የማንኛውንም ተመራማሪ ሕሊና ማጥገብና ማርካት የሚችል ሌላ ነገር አይገኝም ። አንድ ነቃፊም «ዮናስ ተኝቶ ሳለ ሌሊት በቅዠት ያየውን ነገር ተነሥቶ ሕልሙን ጻፈው እንጂ የሆነ ታሪክ አይደለም» ብሏል ።

ሌላው ተጠራጣሪ ደግሞ «የዮናስ መጽሐፍ በሞላ ሰው ሠራሽ ነው እንጂ ታሪካዊ ነገር አይደለም» ብሏል ። አንደኛው ግራ ገብ አሳቢ «ደግሞ ዮናስን ከመርከቢቱ አውጥተው በጣሉት ጊዜ መርከቢቱን ትከተል የነበረችው ሌላ መርከብ ተቀብላው ነበር ። ይህች ሁለተኛዪቱ ተከታይ መርከብም በዓሣ ቅርጽ የተሠራች መርከብ ነበረች ፣ ስለዚህ በመጀመሪያዪቱ መርከብ የነበሩት ተሣፋሪዎች ዮናስን ልትታደግ የመጣችው መርከብ በተቀበለችው ጊዜ የቀላይ ዓሣ የተቀበለው መስሎ ታያቸው» "ብሏል ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በግልጥ አምላክ ያሰናዳው ዓሣ ዮናስን ዋጠው» ይላል ።

አሁን «እግዚአብሔር ዓሣ አሰናዳ» የሚለውን ዐረፍተ ነገር ልብ ታደርጉ ዘንድ እናስታውሳችኋለን ። በጠቅላላው ክርክሩ ሁሉ በእነዚህ ቃላት ላይ ማረፍ ይገበዋል ። ጥያቄውም አንድን ሰው በከርሱ ተቀብሎ ሰበ ሁለት ሰዓታት ሙሉ ማስተናገድ የሚችል ዓሣ እግዚአብሔር ሊያዘጋጅ ይቻለዋል ? የሚለው ነው ።

እግዚአብሔርም ይህን ማድረግ ካልቻለ እንግዲህ ከሰው ያነሰ ነው ማለት ነው ። አሁን በቅርቡ የመሐንዲስነት ጥበብ ያጠኑ ሥጋ ለባስያን ሰዎች አንድ የብረት ዓሣ ማገጣጠም ችለው ነበር ። ኻያ የሚሆኑ ሰዎችም በዚሁ በብረት ዓሣ ውስጥ ገብተው ኻያ ቀኖችና ኻያ ሌሊቶች በውሃ ውስጥ ቆዩ ። በዚሁ ጊዜ መጨረሻ ላይም ወደ የብስ ወጥተው ተፈላጊውን ምግብና ንጹሕ አየር ለስንቅ ወሰዱ ። ይህ የብረት



ዓሣም ዕረፍት እንዲያደርጉ ከየብስ ላይ አሳረፋቸው ። እንደገናም ደግሞ ሌሎች ኻያ ሰዎች በዚሁ የብረት ዓሣ ውስጥ ገቡና ወደ ባሕሩ ቀላይ ወረዱ ። ይህን ሰው ሠራሽ ዓሣም የባሕር ውስጥ መርከብ ብለው ሠየሙት ። እንደዚህ ያለ ዓሣ በጥበባቸውና በብልሃታቸው ማገጣጠም መቻላቸውም ደግም ምንም አጠራጣሪ ነገር አልሆነም ። እንደዚህ ያሉ ሰው ሠራሽ ዓሦችም በዛሬው ጊዜ በጣም የተለመዱ ናቸው፤

ሰዎችም የሰው ሥልጣን እነዚህን ሰው ሠራሽ ተአምራት ለማድረግ መቻሉን ሲያዩ የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ኃይል ለማየትና መገንዘብ አለመቻላቸውን ስናስብ እንዴት የሚያስገርም ነገር ነው ! ። እንዲያውም አምላክ በሥልጣኑ ከዓሦች ሌላ ሌሎች ፍጥረታትን ፈጥሮ እናያለን ። በዮናስ ታሪክ ውስጥም አንዲት የወይን ተክልና እንደሁም በተለይ የእሷ ጸር የሆነች ትል በእግዚአብሔር ሥልጣን መዘጋጀታቸውን እናያለን ።

ያለ ወቅቱ ኃይለኛ ምሥራቃዊ ነፋስ ነፍሶ ነበር ። ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ አምላክም ዓሣን ፣ ትልንና ፣ የወይን ተክልን ፣ አዘጋጀ ።

ከጥቂት ዓመታት በፊትም በደቡባዊ ክፍለ ሀገር ጥንታውያን ታሪካውያን ነገሮችን ለመቆፈር ሄደን በነበረበት ጊዜ በዘመኑ ጥበብ (ሳይንስ) ረገድ የታወቀ ችሎታ ከነበረው ሰው ጋር ጓድ ለመሆን ዕድል አጋጥሞን ነበር ። ይህ ሰውዬም ብልህና አስተዋይ አሳቢ ስለ ነበረ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይተዋወቅ ወይም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ግድ ያልነበረው ሰው ነበር ። ቀትር ላይ ቀኑ በጠረረ ጊዜ ከፀሐይ ሐሩር የተነሣ ተላውሶ ምንም ሥራ ለመሥራት ባለመቻሉ በበረሃው ከነበረው ቁጥቋጦ ሥር ቁጭ ብለን ብዙ የሓሳብ መለዋወጥ አደረግን ።

ከዕለታት አንድ ቀንም የምንለዋወጠው ጭውውት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አመራ። በዚሁ ዕለትም የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ይህን ምድርን ቆፍሮ በሚያጠናው ጥበብ ረገድ ሊቅ የነበረ ጓዱን «እንዳንተ ያለ ብሩህ የሆነ አእምሮና የማስተዋል ተሠጥዎ ያለው ሰው እንዴት ክርስቲያን አልሆንህም» ? ሲል ጠየቀው ።

ሊቁም መልሶ በቅንነት እነጋገር «ክርስትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር መውደቅ ወይም ደግሞ ጸንቶ መቆም ይገባዋል ። ምንም እንኳን ክርስትና ውብና ሕሊናን መሳብ የሚችል መስሎ ቢታይም ፣ ከቶ ክርስቲያን አልሆንኩም ፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን እንደማይሳሳትና በእግዚአብሔር መንፈስ ቀስቃሽነት የተጻፈ መጽሐፍ ነው ብላችሁ እናንተ ክርስቲያኖች ስለምትፋለሙለት ነው ። ስለዚህ እኔ ልቀበለው አልቻልኩም" ። ብሎ አስረዳ ።

ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታውያን ቁም ነገሮችም እንደ እሱው ያለ ዝንባሌና አስተያየት ያለን መስሎት ስለ ተናገረ ፣ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ መልሶ «ባብሆይ ፣ ኢየሱስ ክርስቶስና መጽሐፍ ቅዱስ ጸንቶ ጎን ለጎን መቆም ወይም ደግሞ ተገዳድፈው አንድ ላይ መውደቅ ይገባቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ዋጋም መቀበል ይገባል ። የሆነ ሆኖ በመጽሐፈ ዘፍጥረት ተመዝግበው የሚገኙት ታሪካውያን ቁም ነገሮች ሁሉ ሊታመንባቸው ይገባል ፤ እነሱም የማስረጃቸውን ሸክም በየገጹ አዝለዋል፤ ተቃዋሚ ወገን ለሚያቀርበው ክርክርም እንዳቀራረቡ በማስረዳት ይመልሱለታል ። ስለዚህ በመጽሐፈ ዘፍጥረት ስለ ጥፋት ውሃ ተመዝግቦ የሚገኘው ታሪክ እውነተኝነቱ በማያጠራጥር አኳኋን በሦስት ዕውቅ በሆኑ ዘመናዊ የሳይንስ ዘርፎች አስረጅነት ላይ የተመሠረተ ነው ። ስለዚህ ጉዳይ ያለው ምስክርነት ብዛትና ዝርዝርም በጣም ሰፊ በመሆኑ በብዙ መጻሕፍት ስለዚሁ አርዕስተ ቁም ነገር ተዘርዝሮ ሊጻፍ ይቻላል ፤ ተጽፏልም ።

ስለዚህ አሁን ስለዚሁ ጉዳይ በዚህ በአጭር ምዕራፍ ውስጥ በዝርዝር ለመጻፍ ጊዜ ስላልፈቀደልን ስለ ሦስቱ ሳይንሶች ጉዳይ በማሳጠርና በማጠቃለል ከዚህ በታች እንደ ተጻፈው እናስረዳለን ።

ከእነዚህ ከሦስቱ ጥበቦች (ሳይንስ) የጥፋት ውሃ በዓለም ላይ መሆኑ እርግጠኝነቱን የሚያስረዳው ስለ ሰው ዘር ባህል የሚያጠናው ጥበብ (ኤትኖሎጅ) የገለጠው ምስክርነት ነው ። ይህ ጥበብም ዛሬ በዓለም ላይ ስለሚገኙት ልዩ ልዩ የሰው ዘር ሁሉ የሚመረምርና የሚያጠና ጥበብ ሲሆን ስለ ባሕላቸውና ስለ እያንዳንዱ ጐሣ መሠረተ መነሻና አንድን ጐሣ ከሌላው ለይቶና አበጥሮ በመካከላቸው ያለውን ልማዳዊ ይዞታ ጠንቅቆ የሚያስረዳ ጥበብ ነው ። ስለ ሰው ዘር ጉዳይ መርማሪ ሊቆችም በሁለት መሠረታውያን ቁም ነገሮች ላይ ተስማምተዋል ።

ሌላውም መደምደሚያ ነገር ሰዎች በሰፊው ተለያይተው ቢኖሩም አንድ መሠረተ መነሻ ያለው አፈ ታሪክ ወይም እምነት ሲየያዝ መጥቶ የሚደርሳቸው ነገር ነው ፤ ይህ በየበኩላቸው ያላቸው አፈ ታሪክም አንድ እርግጠኛ ታሪካዊ ነገር ለእምነታቸው መሠረት የሚሆናቸው ነው፤ በዓለም ላይ ከሚኖሩት ማንኛውም ጎሣ ወይም ነገድ ቢሆን በኖኅ ዘመን ስለሆነው የጥፋት ውሃ የማይተርክና የማያወጋ ጎሣ ስለ አለመኖሩም ማናቸውም ስለ ሰው ዘር ጉዳይ የሚያጠናው አዋቂ ተቃውሞ ወይም ክዶ አያውቅም ። እንግዲህ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እርግጠኛ ከሆነ ዘንድ ፤ ይህ እርግጠኛ ነገር ሊታሰብበት ይገባል ። በዓለም ላይ የሚኖሩት ጎሣዎች ሁሉም ከኖኅ ጋር በመርከቡ ከዳኑት ልጆቹ በአንደኛው ሐረግ ትውልድ ዘርፍ ዓለምን ስለ ሞሏት እነሱም በየፊናቸው ለዘሮቻቸው ተፈላጊውን መሠረታዊ ታሪክ በዝርዝር አስተላልፈውት ይገኛል ።

የኖኅ ልጆች ከወለዱአቸው በኋላም ፤ ከነዚህ ጎሣዎች አንዳንዶቹ ሠልጥነዋል ፤ አንዳንዶቹም ደግሞ ደንቍረዋል ፤ ሆኖም ስለ ጥፋት ውሃ ታሪክ በየበኩላቸው ይተርካሉ ። በዚሁ ታሪክ ለሚደሰት ትጉሕ ተማሪም ከሠላሳ ሦስት የማያንሱ ከያንዳንዱ ጎሣ የተጻፉ ነገሮች ስለሚገኙ ዛሬ ከሚገኙት ሕዝቦችና ጎሣዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ ታሪኩን ይበልጥ ሊረዳ ይችላል ። ከነዚህ ቍጥራቸው በብዛት ከሚገኘው ምስክሮችም የግብፃውያንና የእስካንዳናቭውያን መዝገቦች ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቦ ስለ ጥፋት ውሃ ከሚተረከው ታሪክ



ጋር በፍጹም አይመሳሰሉም ። የእስካንዳናቭውያንና የግብፃውያን ታሪኮችም በውሃ ምክንያት በከፊል በምድር ላይ ጥፋት ደርሷል ማለትን ሲገልጹ ፤ በአማክልቱ ቀጥተኛ አፈጻጸም የሆነ ጥንታዊ አድራጎት ነው ይላሉ ። ስለዚሁ ዝርዝር መግለጫም በጥንቃቄ ምርመራ ሲደረግ ካሁኑ ሕዝቦች አምስቱ ብቻ በመርከብ ሳይሆን በሌላ አኳኋን ከጥፋት ውሃ ስለ ተረፉት ሰዎች የደረሳቸው አፈ ታሪካዊ ዘዴ እንደሚገልጠው ሁሉ ከመነሻው ጋር የተያያዘ ዝርዝር አላቸው ። ከዚህም ቍጥር ከነዚህ ሕዝቦች አንደኛው ስለ ሰው ዘር ከጥፋት ውሃ መትረፍ ምንም መግለጫ አይሰጥም ። ሌሎች ሦስቱ ግን ስለ ጥፋት ውሃ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኘው ታሪክ በከፊል ይሰጣሉ፤ ያጸናሉም ። ከነዚህም ሦስቱ መግለጫዎች ስለ እንስሳት መትረፍ ጉዳይ ምንም መግለጫ አይሰጡም ፤ አንደኛውም፤ በኦሪት ዘፍጥረት እንደሚገኘው ሁሉ ስለ ጥፋት ውሃ ታሪክ በከፊል ተመሳሳይ የሆነ ምስክርነት ይገኝበታል ። በነዚህም ግልጥ በሆኑ መግለጫዎች ከሦስቱ በቀር ሌሎቹ ሁሉም መርከቡ በአንድ ተራራ ላይ ማረፉን ይተርካሉ ። ከተመዘገቡት ታሪኮች አራቱ ርግብዋ ስለ ውሃው መጕደል ተልካ ወጥታ ለተረፉት ሰዎች የምሥራች ስለ ማምጣቷ ምንም አይተርኩም ። ከነዚህ ከተመዘገቡት ታሪኮችም በተረፉት ሰዎች ላይ የአምላክ ሞገስ ስለ መኖሩ አይገልጡም ። ሁለቱ ብቻ ደግሞ የዳኑት ሰዎች ከመርከቡ እንደ ወጡ ለአምላካቸው ስለ መስገዳቸው አይገልጡም ። ስለዚህ ስለ ሰው ዘር ልማዳዊ ባህል የሚያጠናው ጥበብ በዝርዝር ስለሚሰጠው ምስክርነት በዚህ አጭር በሆነ ምዕራፍ ውስጥ ሙሉ የሆነ ዝርዝር መግለጫ ለመስጠት አለመቻሉ ግልጥ በመሆኑ በጥቂቶቹ ብቻ ራሳችንን ማርካት እንችላለን ። የፊንቄአውያን ታሪክም ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር ይቃረባል ። ከጥቂት ጊዜ በፊት በነዚሁ ደሴቶች ላይ በነበርንበት ጊዜ የሽማግሌዎች ተረትና የሀገር ተወላጆቹ የአፈ ታሪኮች አሰጣጥና አሰነዛዘራቸው በጣም አስደስቶን ነበር ። በሐዋይ ደሴቶች ላይ የጥንት ተረቶችን ለማጠራቀም በመቻላችን ዕድለኞች ሆነን ነበር ፤ እነሱም አንድ የቤተ ክርስቲያን ወገን የሆነ ቄስ የጻፋቸው ነበሩ ፤ በስድስተኛው ሾሊዮም ሁለተኛ መጽሐፍ ፤ ሦስተኛ ተከታታይ ቍጥር ምዕራፍ ሁለት ላይ ጥንታውያኑ ፊንቄአውያን ስለ ጥፋት ውሃ ያላቸው ታሪክ ተጽፎ ይገኛል ።

በዚሁ ታሪክ ውስጥ የሚወሳው ጀግናም ስሙ ኑ-ው ይባላል ፤ ይህም (ለኖኅ የተቃረበ ስም ነው) ከአማልክቱም ኬን ለተባለው ትእዛዛት ሁሉ ታዛዥ በመሆን ኑ-ው በላዩ ላይ አንድ ትልቅ ቤት ያረፈበት ታላቅ መርከብ ሠርቶ ስሙም ዋአ አሁላው ይባል ነበር ። ይህን ሥራ ለመሥራትም ባለቤቱ ሊ. ሊ. ኖኤ የተባለችው ረድታው ነበር ፤ ስለዚህ የጥፋት ውሃ በወረደ ጊዜ በሠራው መርከብና ቤት ገብቶ በመንሳፈፍ በጥፋት ውሃ ላይ ያለ ምንም ሥጋት በመፋዋለል ጋለበበት ። የጥፋት ውሃም በጎደለ ጊዜ ኬን ኩና ሎኖ የተባሉት ሦስቱ አማልክት ወደ መርከቡ ውስጥ ገቡና ኑው እንዲወጣ አዘዙት ። እሱም እንደ ታዘዘው በወጣ ጊዜ በሐዋይ ደሴት ማውና ኬያ ከተባለው ኮረብታ ላይ ማረፉን ተረዳው ። ከዚያም በአንድ ዋሻ ውስጥ ይኖር ስለ ነበረ ዋሻውን በባለቤቱ ስም ሊ. ሊ. ኖኤ ብሎ ሠየመው ይባላል ። ለዚህም ማስረጃ ይሆነን ዘንድ ዋሻው ስምዋን እንደያዘ እስካሁን ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

ወሮች ይጠቅሳል ፤ የፀሐይ ዝንባሌም በሰሜን በኩል በኻያ አንደኛው ሚዛን ላይ ሲሆን ከትክክለኛው ቀትር በአሥራ አንደኛው ሚዛን ላይ ትገኝ ነበር ማለት ነው ።

ምንም የመሣሪያ ድጋፍን ያላገኘ ዓይንም በሰማይ መኻል (አጋማሽ) (ቻትሲ) ላይ መሆንዋን አረጋግጦ ማወቅ አይችልም ። ይህችም ዕለት በጥቅሱ ውስጥ አልተወሳችም ። ዳሩ ግን ዘመንን ለሚቆጥርና ለሚለካ ጥበብ (ክሮኖሎጂ) ይህ ጉዳይ በጣም ቀላል ነው ፤ በጦርነቱ ጊዜ የሆነውን እርግጠኛ ታሪካዊ ነገር በሳይንስ ጥበብ ተንትኖ ለማረጋገጥ ይቻላል ።

ስለዚሁም አስደሳች ጥናትና ምርምር በፕሮፌሰር ቶተን እንደ ተብራራው ሁሉ ይህ ጦርነት የሆነው በዕብራውያን አቆጣጠር ከወሩ በኻያ አራተኛውና በኻያ አምስተኛው ዕለታት ላይ የሆነ መሆኑን በሒሣብ ተንትኖ ሲያረጋግጥ በአንድ መቶ አሥራ ሦስተኛውና በአንድ መቶ አሥራ አራተኛው የቀን መቍጠሪያ ዕለት ላይ መሆኑን ለይቶ ገልጧል ። የዚያች ወር ኻያ ሦስተኛ ዕለትም በበጋ ወራት ፀሐይ ከመካከለኛው መሥመር (ኤኩዩተር) ርቃ የምትገኝበት ዕለት መሆኑን ለማስረዳት ፈለገ ።

ስለዚህ እንደ ኤውሮፓ ዘመን አቆጣጠር የቀኑና የሌሊቱ ጊዜ ትክልል ከሚሆንበት ከአሥራ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት ዓመተ ምሕረት ሐጋይ ወር አንስቶ ጦርነቱ እስከ ሆነበት ዕለት ድረስ ወደ ኋላ በሒሣብ ሲቆጠር) በፀሐይ አቆጣጠር ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሰባ ዓመታት መሆኑንም ጭምር አስረድቶ ነበር ።

ነገር ግን በዚሁ አኳኋን ሒሣቡን ማውጣቱ ጨረቃ በአየሎን ሸለቆ መኻል እንደ ነበረች ማይገምት በአየሎን ከተማ አናት ላይ እንደነበረች በመቈጠሩ ይህ ሒሣብ ተጣርሶ ያሳሳተውም በስም አንድ በመሆኑ ምክንያት እንደ ነበረ ተገልጧል ።

ጥንታውያንም ስለ ፀሐይ ፤ ጨረቃ ፤ ከዋክብትና ፕላኔቶች የሚያጠና ጥበብ (አስትሮኖሚ) ስለ ነበራቸው ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ድረስ ሁኔታዎችን ሁሉ እየመዘገቡ ያኖሩ ነበር ። ግብፃውያንም ፀሐይ ከዓለም አጋማሽ መሥመር እርቃ የምትገኝበትን ጊዜ ሁሉ እየመዘገቡ ያኖሩ ይመስላል ። ከለዳውያንና ሌሎች ጥንታውያን ሕዝቦች ግን አንዳንድ ያልተለመደ ነገር ሲያጋጥምና ጨረቃም በፀሐይና በምድር መኻል አቋርጣ ስታልፍ የሚሆነውን መጋረድ እየመዘገቡ ያኖሩ ነበር ። የጨረቃም ሆነ የፀሐይ ሁኔታዎች ብዙዎቹ የተመዘገቡ መሆናቸው በልዩ ልዩ መርማሪ ቡድኖች ጥረት መረጃዎቹ ተገኝተዋል ። በቀን መቍጠሪያው በኩል ያለውን የዕለታት መለዋወጥ ችላ እንበልና ዘመናትን የሚለካና ዕለታትንም ወደ ሚያጠናው ጥበብ (ክሎኖሎጂ) ተመልሰን በፀሐይ ንቅናቄ ላይ የደረሰውን ትክክለኛ ጥበብ እንከታተል ። ስለዚህ በጥንታውያን ዘመን ከሁሉ መጀመሪያ ሁኖ ወደ ተመዘገበው* መረጃ እንመለስና መነሻችን አድርገን እንጠቀምበት ።



ስለ ፀሐይ ፤ ጨረቃ ፤ ከዋክብት ፕላኔቶችና ስለ ሌሎች ዓለማት የሚያጠናው ጥበብ ያገኘልን ቅድሚያና ትክክለኛ ሆኖ ተመዝግቦ የተገኘው መረጃ ኢያሱ እስከ ተዋጋበት ዕለት ድረስ ተጠንቶ ውጊያው የሆነበት ዕለት ማክሰኞ ላይ መሆኑ በትክክል ታውቋል ። ስለዚህ በመጨረሻ ጨረቃ በፀሐይና በምድር መኻል ስታልፍ ሳለ ፀሐይ ተጋርዳ ከጨለመችበት ጊዜ አንስቶ ውጊያው እስከ ሆነበት ዕለት ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ የታሰበ እንደሆነ ፤ ውጊያው የሆነበት ዕለት ረቡዕ ላይ ሆኖ እናገኘዋለን ። በአደረግነው መደምደሚያ ሀሣብ ላይም አንድ ዓይነት ስሕተት ማድረጋችን ሲሰማን ደግሞ ፤ እንደ ገና ወደ ኋላ ተመልሰን መቍጠር ስንጀምር ፤ በመጀመሪያ የተሰጠው መደምደሚያ ሀሣብ ትክክለኛ ሁኖ እናገኘዋለን ። ይህ ታሪካዊ ነገር ከሆነበት ጊዜ አንስተን የመረመርን እንደሆነም እንደ ገና ውጊያው የሆነበት ዕለት እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ሐምሌ ኻያ ሁለት ቀን ላይ ይሆናል ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ እንደ ኤውሮፓውያን አቆጣጠር ከአሥራ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ስድስት ዓመተ ምሕረት አንስተን ኢያሱ አምስቱን ነገሥታት ድል እመታበት ዕለት ድረስ የቆጠርን እንደሆነ አሁንም ሐምሌ ኻያ ሁለተኛው ዕለት ረቡዕ ላይ እንደርሳለን ። እንዲህ ማለትም የወሩ ዕለት ያው ነው ማለት ሲሆን የሳምንቱ ዕለት ግን ይለያያል ማለት ነው ።

በአእምሮአችንም መወጠን በምንችለው መጠን በማንኛውም በኩል ሒሣብ ብናደርግና እንደ የችሎታችን መጠን ብንመራመር ጊዜን በሚለካና ዓመተ ምሕረትን በሚወስን ጥበብ (ጥናት) መሠረት ተመዝግበው በሚገኙት መረጃዎች ሁሉ ብንጠቀምባቸውና ብንሠራባቸው ፤ በዚያው ሳምንት ውስጥ አንዲት ዕለት ጠፍታ እናገኛለን ። በጊዜው ተመዝግቦ በተገኘው መረጃም ትክክለኛው በፀሐይ የደረሰው ሁኔታ በጥንቃቄ ተመዝግቦ ይገኛል ። እነዚህንም የተገኙትን ልዩ ልዩ መረጃዎች ስናገናኛቸው የዚህን ውጊያ ጊዜና ዘመን ገልጸን ማስረዳት እንችላለን ።

ይህ ታሪክ በፀሐይ የደረሰውን ሁኔታ በመያዙ ሙሉ በሙሉ የዓይን ምስክር በሆነ መዝጋቢ የተጻፈ ለመሆኑ ከልብ እናምናለን ። በሳይንስ በኩል እንደዚህ ትክክለኛ የሆነ የተዋኻደና የተጋጠመ ነገር በኋለኛው ዘመን ተነሥቶ አንድ ጸሐፊ የጨመረው ነው ማለትና ፤ በሳይንስ ረገድ ትክክል ሆኖ የተገኘውን የፀሐይና የጨረቃን አቀማመጥ ያውቃል ማለት ሐሰተኛነቱን ጥቅሱ ራሱ ሊያስረዳው ይችላል ። ዘመናዊው የፀሐይ ፤ የከዋክብት ፤ የምድርና በጠቅላላው የዓለማት ሁሉ ጥበባዊ ጥናት እስኪ ወለድ ድረስ ይህ ጸሐፊ አይችልም ነበር ። ማንኛውም በኋለኛው ዘመን ይህን ጥቅስ ጨመረ ብሎ የታሰበው ጸሐፊም ፤ ይህን በግምት ወይም በመላ ማወቅ አይችልም ። ይህ በቅደም ተከተል ተያይዞ የተረጋገጠው አቀማመጥም እያንዳንዱ ጨረቃ ባመት ውስጥ በትክክለኛ መጠን አንድ ዕለት ላይ ሲውል ነው ።

ስለዚህ በኋላ የተጨመረ ነው በማለት አንካሳውና ደካማው የፍጡር ድንጋጌ ይንካከታል ። ከሐዲነትን ለመደገፍ ሲባል አንካሶች እንደሚደገፉት እንደ በለ ባላ ምርኩዝ የሚመስል ሲሆን ይህም ደግሞ ተጣይና ወዳቂ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው ፤ ስለ ኢያሱ ዕውቀት ውሳኔ ነው ።

ኢያሱ ፤ ፀሐይ እምብርት መሆንዋን ለማወቁና ላለማወቁ ለይተን ማወቅ አንችልም ። ዳሩ ግን ቢያውቅም ባያውቅም እኛን የሚያሳስበን አይደለም ። ይህ ታሪክም የተጻፈው በኢያሱ ዕውቀት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አነቃቂነት የተጻፈ ነው ። በኢያሱ መሣሪያነት ብቻ ራዕዩ ተመዝግቦ እንዲቆይና ለተተኪው ትውልድ ሁሉ እንዲተላለፍ ያደረገው ማናቸውንም ነገር ጠልቆ የሚያውቀው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ።

ሁለተኛው ፤ የተሣሣተው ሐሳብም ኢያሱ መሠረተ ቁም ነገሩን ለመግለጽ ሲል የተጠቀመበት ቃል ነው ። ኢያሱም ፀሐይና ጨረቃን ጸጥ ብላችሁ ቁሙ አላለም ። እናንተም እንደምታውቁት ሁሉ ኢያሱ በእንግሊዝኛ አልተናገረም ነበር ። ኢያሱ የተናገረው በዕብራይስጥ ሆኖ ይህ ጥቅስ በመጀመሪያ የተጻፈው በዕብራይስጥ ነው ። ወደ እንግሊዝኛ ለመተርጎምም ከመሠረተ መነሻው መተርጐም ነበረበት ። ስለዚህ ኢያሱን ለመንቀፍም ሆነ ለማረም ከመጣደፍ በፊት ፤ የገዛ ቋንቋውን እንመልከትና ምን እንዳለም እንረዳ ። አሁን ከምንናገርበት ጥቅስ ሐሳብን ወደ አንድ ዕብራይስጥ ቃል መምራት ብቻ ይበቃናል ፤ ኢያሱ በተናገረ ጊዜ ፀሐይ ፤ "ዳማም,, ሁኚ አለ ።

,,ዳማም,, የሚባለው የዕብራይስጥ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ በጠቅላላው ኻያ አንድ ጊዜያት ሐሳብ ተገልጦበት ሲገኝ ፤ በየትኛውም ሥፍራ ቢሆን ጸጥ ብሎ መቆም ተብሎ አልተተረጐመም ፤ እንግዲህ ይኸው የእብራይስጥ ቃል ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎም ''ረጋ'' ማለት ተብሎ ይተረጎማል ማለት ነው ።

በዕብራይስጥ መቆም ማለት ,,አማድ,, ማለት ነው ፤ አማድ የሚባለውም ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ መቶ ጊዜያት ሲገኝ የዘወትር ትክክለኛው ትርጉሙ መቆም ወይም "ረጋ ብሎ» «መቆም» ማለት ነው ።

እሱም ፤ በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አሥር ከስምንተኛው ቍጥር ላይ ይገኛል ። ጥቅሱም እግዚአብሔር ኢያሱ ድል መንሣትን የሚያገኝ ለመሆኑ ተስፋ በደረገለት ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ''ከእነሱ ፤ አንድም ሰው ከፊትህ አይቆምም,, (አማድ) ይላል ።

ስለዚህ ኢያሱ ፀሐይን በተናገረ ጊዜ «ፀሐይ ረጋ በዪ» አለ ። እያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱስ በሕዳጉ ያለው ንባብ ረጋ ያለ በመሆኑ ይህንኑ የመሰለ ትርጓሜ ይሰጣል ። ያለን መጽሐፍ ቅዱስ ሕዳግም ይህን ትርጉም ይሰጣል ። የየራሳችሁን መጽሐፍ ቅዱስ ተመልከቱና ሕዳጉ ምን እንደሚል እዩ ። እንዲህ መባሉም ለመደገፍ ሲባል ነው ። አሁን በዚህ ጩኸት እውነተኛውን ጉዳይ ማየት ትችላላችሁ ። ኢያሱም የፀሐይን ብርሃን አልፈለገም ነበር ። ታላቁ ችግሩም የፀሐይ ሐሩርና ግለት ነበር ።



እሥራኤላውያንም ግሩም የሆነ የግዴታ ግሥጋሤ በማድረግ ከጊልገል ተነሥተው ጠላቶቻቸው በገዛ ከተማቸው በመከላከያ ሥፍራዎች ላይ ሳሉ ሳያስቡት በስተኋላ ደርሰው ማባረር እንዲችሉ በአሥር ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ከዐርባ ምዕራፎች (ማይል )በላይ ተጕዘው ነበር ። ከባድ የሆኑት የብረት መሣሪያዎች ፤ ጦሮች ፤ የሚወነጨፉ ድብልብል ደንጊያዎች ፤ ቀስቶች ከነጦሮቻቸውና በጥንት ዘመን ይጠቀሙበት የነበረውን ተፈላጊ የጦር መሣሪያ ሁሉ ተሸክመው ይህን ያህል ርዝመት ያለው ጎዳና አቋርጠው ተጉዘው ምንም ዕረፍት አላደረጉም ነበር ፤ ከእዚሁ ካሥር ሰዓታት የግሥጋሤ ጕዞ በኋላ እንደ ደረሱም በቀጥታ ውጊያ ገጠሙ እንጂ ዕረፍት አላደረጉም ነበር ። ምንም ዕረፍት ሳያደርጉ ሰባት ሰዓታት ያህል ተዋጉ ፤ ከዚያ በኋላ ግን ጠላት መመከት ባለ መቻሉ የጠላት ጦር ሠራዊት ተፈታ ።

ዕለቱም እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ሐምሌ ፳፱ ዕለት ቀትር ሰዓት ላይ ነበር ፤ ስለ ጊዜ ጉዳይ ከሚያጠናው ጥበብ (ሜቴዮሮሎጂ) ላይ ተመዝግቦ ከተገኘው ማስረጃ እንደምንረዳው ሁሉ በፓለስቲን አገር የሙቀት መለኪያ ሚዛን (ቴርሞሜትር )በሐምሌ ወር በጥላ ውስጥ የሚያሳየው ከአንድ መቶ አምስት እስከ አንድ መቶ ኻያ ደረጃ (ዲግሪ) ድረስ ይሆናል ። ለአሥር ምዕራፎች (ማይልስ) ያህልም ምንም ጥላ አልነበረም ፤ የጭፍሮቹም ተግባር እነዚያን የተባበሩትን የአምስቱን ነገሥታት የጦር ሠራዊቶች ማጥፋት ነበር ። እነዚያ የተባበሩት የጦር ሠራዊቶችም መመከት ወይም መከላከል ትተው በሽሽት ላይ ነበሩ ። የእሥራኤላያውን ወታደሮችም ሌሊቱን ሲጓዙ አድረው ጐሕ እንደ ቀደደ ውጊያ ገጠሙ ፤ የጠላት የጦር ኃይል ተፈትቶ ሽሽት የጀመረውም ቀትር ላይ ነበርና ዕረፍት አድርገው አንዳችም ምግብ አላገኙም ነበር ፤ እነሱም የጨበጣ ጦርነት ሲዋጉ በመዋላቸው ዝለውና ተዳክመው ነበር ።

የዛለው የእሥራኤል ሠራዊትም አሰቃቂ ሐሩር ጎድቶት ስለ ነበረ ጦረኞቹ በነበሩበት ሥፍራ ሁሉ ተፈነገሉ ፤በሽሽት ላይ የነበሩትን የጠላት ወታደሮችም አባርረውና አሳድደው ይበልጥ ያጠቁአቸው ዘንድ ምንም ብርታት አልነበራቸውም ነበር ።

እንዲህ ከአፋፍ ላይ በተደረሰበት ሰዓትም የኢያሱ ጸሎት ቃል በቃል ሲተረጎም «አንቺ ፀሐይ ረጋ በይ» ወይም ፀሐይ «ፀጥተኛ ሁኚ» አለ ። ጸሎቱም በቅጽበት መልስን አገኘ ።

ጥቁር ጨለማም ፀሐይን ጋረዳት ፤ የበረዶ ውሽንፍርም ዘነመ ። እንዲህም የሆነው በፓለስቲን የዓመት ወቅት ውስጥ ከቶ ዝናም አካፋቶ እንኳ በማያውቅበት ወቅት ነበር ፤ በፓለሲቲን አገር የመጀመሪያው የክረምት ዝናም የሚጀምረው በኛ በኅዳር ውስጥ ነው ። ዝናሙም ቀላል ዝናምና ጉርምርምታ ጭምር ነው ። ክረምቱም የሚያባራው በሚያዝያ ወር ነው ።

ከታህሣሥ እስከ የካቲት ድረስ የሚዘንመው መጠንም ከኻያ እስከ ሠላሳ አጽቅ (ኢንች) ያህል ብቻ ነው ። በበጋ ወራት ግን አንዲት ጠብታ ስንኳ አያካፋም ።

www.ethiopianorthodox.org

| ተራ | ገጽ | መሥመር | ግድፈት ። | እርም ። |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ፲፩ | ፩ | ዓላማትን | ዓለማትን |
| ፪ | ፲፫ | ፮ | ወጣቶችም | ወጣቶችን |
| ፫ | ፲፮ | ፳፮ | ፪ኛ ጴጥ ፫ ፲፬–፲፮ | ፪ኛ ጢሞ ፫ ፲፬–፲፮ |
| ፬ | » | ፴፭ | አዲስ ኪዳን ወይም | በአዲስ ኪዳን ወይም |
| ፭ | » | » | የምማራቸው | የምንማራቸው |
| ፮ | ፵፰ | » | ግደግ ይገባል ብሎ እንደመጠየቅ | ግደግ እንደሚገባ ይመክረዋል |
| ፯ | ፷፰ | ፴፬ | በርዕ | በዕርዕ |
| ፰ | ፸ | ፳፭ | ደመ ግብ | ደመ ገብ |
| ፱ | ፸፩ | » | ከሚጠናው | ከሚያጠናው |
| ፲ | ፸፭ | ፲፮ | በ፱ኛናው | በ፱ኛኛው |
| ፲፩ | ፸፰ | ፳፩ | የሚጀምር | የሚጀመር |
| ፲፪ | » | ፳፭ | ከተራጂዎች | ከተራራዎች |
| ፲፫ | ፺፩ | » | ከመጠቅለያው | ለመጠቅለያው |
| ፲፬ | ፻፩ | ፭ | የሚተርፉቸው | የሚተፋቸው |
| ፲፭ | ፻፫ | ፲፭ | ሐይድሮጅም | ሐይድሮጅንም |
| ፲፮ | » | ፳፮ | እየተንደቃደቀ | እየተንደቀደቀ |
| ፲፯ | ፻፬ | ፲፫ | የቁመቱ ደረጃ | የሙቀቱ ደረጃ |
| ፲፰ | ፻፷፫ | ፴፮ | ለማያነብ | ለሚያነብ |

www.ethiopianorthodox.org